# የሚገላግለን ሸዋን ራሱን የቻለ
# ክልል ማረግ ነው!

ሰርፀ ደስታ

September 14, 2018

በጅምላ እያጨቁን እነሱ ይጠቀሙብናል! የኦሮሞ ፖለቲካ በአለፉት 50 ዓመትና ከዚያም በላይ ጥላቻና ዘረኝነት ላይ ያተኮረ መሆኑ ዛሬ ብዙ የሚባለውን የኦሮሞ ሕዝብ በዚሁ የጥላቻና ዘረኝነት አረንቋ ውስጥ ከቶ ከሌላው ጋር መኖርን አስጥሎት ለብዙዎች ስጋት ሆኗል፡፡ እውነቱን እርግጥ አድርገን ሳናወጣና በትክክል መሠረት ላይ ሳንቆም እከሌን ይከፋዋልና በሚል በመደባበስና በመላላስ የትም እንደማይደረስ ግልጽ ነው፡፡ የብሔር/የዘረኝነት ፖለቲካ የሚባለው በሁሉም ነበረ፡፡ ግን የዘረኝነት ፖለቲካን እንደ ኦሮሞ ፖለቲከኞችና አክቲቪስት ነን ባዮች ጫፍ ያደረሰው የለም፡፡ ዛሬ ኦሮሞ በእነዚህ ጥላቻና ዘረኝነት በበከላቸው ተውጦ ሰላማዊና ከሌላው ጋር መኖርን የሚፈለገውን ሕዝብ ሙብቱን ገድበውታል፡፡

አሁን አሁን በአማራ ዘረኞች(ብሔረተኞች) የሚታየው ቆይቶ ዛሬ ኦሮሞ የደረሰበት የዘርና የጥላቻ አጣብቂኝ ውስጥ እንሚደርስ አለማስተዋል ስህተት ነው፡፡ እንደውም የኦሮሞ ፖለቲካ የዛሬውን የዘረኝነትና ጥላቻ ደረጃ ላይ ለመድረስ 50 ዓመት ፈጅቶበታል፡፡ የአማራው ግን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሊደርስ እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ ሰሞኑን በፍቃዱ ደግፌ የተባሉ በጣም ትልቅ ተብለው የሚገመቱ ሰው አማራ ማለት መንፈስ ነው! አማራ መሆን የማይመኝ የለም ሲሉን ነበር፡፡ ዶ/ር በፍቃዱ የማከበራቸው ሰው ነበሩ፡፡ እንግዲህ እንዲህ ያለው የዘረኝነት ንግግር የሚነገረው በእድሜም በትምህርትም በብዙ ነገር ተሞክሮም ትልቅ ከሚባሉ ነው፡፡ እንግዲህ ይህ አይነት ዘረኝነት ከእንደነዚህ አይነት ሰዎች ሲጀምር ምን ያህል ተከታይ እንዳለውም አስቡ፡፡ በተመሳሳይ ኢትዮጵያዊነት ይሻለናል ያለው ታማኝ ላይ አማራ ነን ከሚሉ ብዙዎች ምን አይነት ትችትና አልፎም ስድብ እንደደረሰበት ታዝበናል፡፡ ይሄ የሚያስረዳን ውስጥ ውስጡን የአማራ ዘረኝነት ብዙ እንዳደገ ነው፡፡

የአማራን ብሔረተኝነት ከኢትዮጵያ ጋር አይጋጭም ብለው ሊያስተባብሉን የሚሞክሩ ሞኝ ልንሆንላቸው አያስፈልግም፡፡ እናውቃልን አማራው በአለፉት 27 ዓመት ከማንም በላይ በማንነቱ ጥቃት ተፈጽሞበታል፡፡ እራሱንም ለመከላከል ሲደራጅ ለሌላው የተፈቀደ በዘር መደራጀት አማራ እራሱን ሊከላከል ሲደራጅ አልተፈቀደለትም፡፡ የያኔው ራሱን ያደራጀው አማራ በእርግጥም ኢትዮጵያዊ ስለነበር እንዲጠፋም ዘረኞች ሁሉ የተባበሩበት ኢትዮጵያዊነትን መልሶ ያመጣብናል ከሚል ስጋት ነው፡፡

የሆነው ሆኗል፡፡ ዛሬ ደርሰን በስልታዊ መንገድ ኢትዮጵያዊነት ዳግም ውስጥ ውስጡን ጉልበትና መሪዎቹን አግኝቶ በአገሪቱ መንቀሳቀስ ሲጀምር እውንም ወሮበሎቹ የፈሩት እውነት ሆነ፡፡ ገና የኢትዮጵያዊነት ነገር ድምጹ መሰማት ሲጀምር ወሮበሎቹን ብርክ ያዛቸው፡፡ የጎንደሬዎቹ የኢትዮጵያዊነት ጥሪ በከበድ ካሊበር ጥይት ወገቡን እንደተመታ ዝሆን ነበር አይነካ የሚመስለውን የወያኔ ወሮበላ ቡድን ዘጭ ያደረገው፡፡ ቀጥሎ ዛሬ አዳሜ የእኔ የእኔ እያለች የውጤት ባለቤት ልትሆንበት የምትፈልገውን ስኬታማ ለውጥ ቀያሹ ለማ በተምታታ(ዓላማው ግልፅ ያልሆነ ግን ከኢትዮጵያዊነት ውጭ የሆነ) ስሜት ቀድሞ አመጽ የጀመረውን የቄሮ ትግል ገልብጦ የኢትዮጵያዊነት ትግል ቅርጽ አስያዘው፡፡ የጎንደሬዎቹ ጥሪ ከዚህኛው ጋር ሲጣመር ብዙዎች ተቀላቀሉት፡፡

በዛው ልክ ግን ይህ ሂደት ዛሬ የለውጡ ባለቤት እኛ ነን የሚሉትን የኦሮሞ አክራሪዎችን ጨምሮ ብዙዎችን አስደነገጠ፡፡ ቄሮ

በለማ መገርሳ ወደ ኢትዮጵያዊነት ትግል ሀይጃክ ተደረገ! ከቄሮም ቄሮ ግን የሸዋው ቄሮ ድርሻ የላቀና ወያኔን እጁን ጠምዞ ቆጭ ያረጋት ነበር፡፡ ይሄው ቄሮ ነበር ለማን የተከተለው፣ ባሕርዳር አምቦች በሚል ግን አላማው የጎንደሬዎቹን ጥሪ ተቀብሎ ለምክር የሄደው፣ የደሴን ተጫዋቾች ሰንጋ አርዶ የተቀበለው፡፡

በአጠቃላይ እያንዳንዱ የጋራ ግንኙነት እግር ኳስ በሉት እምቦጭ ወይ ሌላ አላማው እምቦጭም እግር ኳስም ሳይሆን ለዘመናት ሆን ተብለው እንዲለያዩ የተደረጉትን የኦሮሞና አማራ ሕዝብን ወደነበረ ወንደማማችነታቸው መመለስ ነበር፡፡ ቀያሹ (ዲዛይነሩ) (ለማ) አላረፈም! ሽማግሌዎችንና አባገዳዎችን፣ ቄሮዎችንም ሰብስቦ ዳግም ባህርዳር ተጓዘ፡፡ዓላማውን ግልጽ አደረገ! ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው አለ! ያኔ ነበር ብዙ ኦሮሞ ዳግም አባቶቹ ያኖሩትን ኢትዮጵያዊነት እንደገና ያስተዋለው፡፡ በተቃራኒው ይህ ዲዛይነሩ ድርጊት ኦሮሞን በዘር ቋት ከተው የእነሱ መነገጃ ሲያደርጉበት የኖሩትን እጅግ አበሳጨ፡፡ ወሮበላው የወያኔ ቡደን መርህ አልባ ሲል ሊያጣጥል ሞከረ፡፡ ድርስ ወሮበላ መርህ ሲገባው አደል፡፡ ከዛን ጊዜ በኋላ በይፋ ኦሮማራ በሚል ትግሉ ወጥ ሆነ፡፡ በፍጥነትም ሌሎች ተቀላቀሉት! ይህ ነው ዛሬ ያለው የለውጥ ስኬት የመጣበት ሂደት፡፡ ከዚህ ውጭ አናምታታ! ይህ ዛሬ የሆነው እንዳይሆን እንቅልፍ አጥተው ሲሰሩ የነበሩ ዛሬ ላይ እኛ ነን ለውጡ እንዲመጣ ያደረግነው ሲሉ አሁንም ፈዘን ልክ ናቸው እንላለን፡፡ አዝናለሁ! እስኪ ከላይ ከጠቀስኩት ውጭ ለውጡን አመጡ የምትሏቸውን ንገረን!
ከላይ እንደጠቆምኳችሁ ከትንንሽ ዘረኝነቶች ወደ ጥምረትና ኢትዮጵያዊነት እያደገ ሲሄድ ምን ያህል ጎልበታም ሆኖ አይነካ የሚመስለውን የወሮበላው የወያኔን ቡደን እንደ ጉም እንዳበነነው አይተናል፡፡ አማራና ኦሮሞ ኦሮማራ መሆን ሲጀምሩ ሁሉም ተቀላቀለ፡፡ ከዛ ወሊጋ የነበረ ቄሮ ጎንደር ላይ ለነበረ ፋኖ መልዕክት ተለዋወጠ፣ መንገድ፣ ሌላም የወያኔ መተንፈሻ ሁሉ በቀላሉ ተዘጋ፡፡ እንግዲህ ይህ ሁሉ አልፈን ድል እኛ እጅ መግባት ሲጀምር ሴረኞች ሌላ ስልት ቀየሩ አሁን ኦሮሞ ያመለጣቸው ለዘመናት በኦሮሞነት ሲነግዱበት የኖሩ ከጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጀምሮ በግልጽ የኢትዮጵያዊነት አዋጅ የመብረቅ ያህል ሆነባቸው፡፡

ስለዚህ በተቻለ መጠን ዘዴ ቀይረው ኦሮሞን አሁንም ኢትዮጵያዊነትን እንዳይቀላቀል ማረግ ግድ አላቸው፡፡ ከፍተኛ ጸረ-ኢትዮጵያ ዘመቻ አደረጉ በዛ ምክነያት አሁንም ኦሮሞን ራሱ ያመጣውን ለውጥ እኳን በአግባቡ እንዳይጠቀም አደረጉት፡፡ ግርግር ለሌባ ይመቻል እንዲሉ በሌላ በኩል ደግሞ የአማራ መብት አስጠብቃለሁ በሚል የአማራ ዘረኞችን በማስተባበር አብን የሚል በድን ተቋቋመ፡፡ አውነትም አብን! ዝም ከተባለ አማራን በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት እንደሚያበነው አትጠራጠሩ፡፡ምን አለፋችሁ አብን የኦነግ ግልባጭ ቢባል ይሻላል፡፡ ዛሬ ኦሮሞ የኦነግ ባንዲራ ላይ ሙጭጭ እንዳለው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ንስር ያለበትን ባንዲራ ካልያዛችሁ እኛ በምንመራበት አካባቢ መኖር አትችሉም የሚሉ እንደሚነሱ ተብቁ፡፡
የኦሮሞ ፖለቲካ ሆን ተብሎ ሕዝብን በጥላቻና ዘረኝነት ለመለየት በሚሰሩ የወሸት ታሪክና ንግርቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የዛሬው አማራ እየሄዴበት ያለው ፖለቲካም እንደዛው ነው፡፡ በተመሳሳይ የኦሮሞም የዛሬው የአማራም የዘረኝነትና ጥላቻ ፖለቲካ እንመራዋለን የሚሉት ምሁር ነን የሚሉ ናቸው፡፡ ዛሬ በአዲስ አበባ የኦነግ ባንዲራ ሕንጻዎቹ ሁሉ ከአልተቀቡ የሚለው ቡድን በዘመናት ኦሮሞን በራሱ አምልኮ ውስጥ እንዲገባ ስለሰራ ነው፡፡ ነገ ንስር በንስር ከአልሆነ የሚል ቡድን አሁን እየበቀለ ነው፡፡
እኛ ኢትዮጵያዊያን ነን፡፡ በእርግጠኝነት እኛገራለሁ! ሁሉም የጄኔቲክ ሴንሰስ ቢሰራ በራሱ ያፍራል፡፡

አማራም ኦሮሞም የሚባል ዘር የለም! የዘረኝነት መንፈስ የፈጠራቸው እንጂ፡፡ ከዚህ በፊት የተወሰነ መረጃ ሰጥቼ ነበር፡፡ ማንም እየተነሳ እንደፈለገው አይዘውረን፡፡ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን እንጂ የኦሮሞ አደለችም፣ የአማራ አደለችም! ወይም እኔ ብቻ የሚል ሌላ! ልብ በሉ በፊትም ተናግሬአለሁ አሁን እላለሁ! ወለጋ ከሀረር ጋር ከሚኖረው ቅርርብ ከጎጃም ጋር ነው ያለው፡፡ እንደውም ጎጃም ለጎንደር ከሚቀርበውም ለወለጋው ሳይቀርብ ባይቀር፡፡ ሸዋ ዛሬ ብዙ የተለያየ ሕዝብ ሆኖ የሚኖርባት ነች፡፡ ጉራጌ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ከምባታም ሌላም፡፡ ይህ ሕዝብ በአብዛኛው ከነገስታቱ ጋር የተያያዘ ሕዝብ ነው፡፡ ዛሬ አዲስ አበባን ፊንፊኔ ከአልሆነች የሚለው ቡድን ስለአዲስ አበባም ሆነ ስለ አጠቃላይ አካባቢው አይገባውም፡፡

አዲስ አበባና አካባቢው የዛሬዎቹ የሚያስቡት ኦሮሞም አልነበረም ሆኖም አያውቅም፡፡ ይህን የሚሉት ታሪኩን ሆን ብለው ከሚኒሊክ ጋር ለማያያዝ ነው እንጂ ፊንፊኔ የተባለ ቦታ ሙዳ ምናምን የሚሉት አልነበረም፡፡ ቦታው ጫካ ነው፡፡ የነበረው፡፡

በአካባቢው ከጥንት ጀምሮ ነገስታቱ ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡ ይሄን ታሪክ የምናገረው ልብ ወልድ አደለም ተጨባጭ ማስረጃ ስላለኝ እጂ፡፡ ለምሳሌ መናገሻ የሸዋ ነገስታት ቦታ ነበር፡፡ እንደውም ዛሬ መናገሻ ሱባ በሚባለው መናፈሻ ነገስታቱ የተከሏቸው ዛፎፍ ሳይቀሩ ምስክሮች አሉ፡፡ ይህ ታሪክ ሲነገር ተረት ተረት ነው ውሸት ነው ሊሉ የሞከሩ አሉ፡፡ ይህን ታሪክ መሠረት አድርጌ እኔው እራሴ አንድ ጥናት አድርጌ ነበር፡፡ አስደናቂ እውነት ይዘዋል እነዛ የመናገሻ ሱባ ጥንታዊ የጽድ ዛፎች፡፡ እድሜ ለቴክኖሎጂ፡፡ ታሪኩ እንዲህ ነበር፡፡ በኋላ ብዙዎች ተረት ያሉት ማለት ነው፡፡

አጼ ዘርዓያቆብ ከወፍ ዋሻ የጽድ ችግኞች (ወፍ ዘራሽ ችግኝ) አምጥተው ተከሏቸው የሚል ነበር፡፡ ይሄን ለማወቅ የእነዚህን ዛፎች ዘረመል(ዲኤንኤ) ከወፍ ዋሻ ዛፎች ዘረመል ጋር ማመሳከር በቂ ነበር፡፡ አስደናቂው አውነት ዛፎቹ አይዋሹም፡፡ የመናገሻዎቹ ዛፎች በእርግጥም የወፍ ዋሻዎቹ ዛፎች ዘመዶቻቸው እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ ይህን የበለጠ ለማረጋገጥ ከጭልሞና ዝቋላ እንዲሁም ከሌሎች ቦታዎች በተመሳሳይ ዘረመል በመውሰድ ለማመሳከር ችያለሁ፡፡ ልብ በሉ በቅርበት ከሆነ የጭልሞና ዝቋላ ጽዶች ለመናገሳ ሱባ ከወፍ ዋሻ ይልቅ ቅርብ ናቸው፡፡ ግን በዘር የመናገሻዎቹ የሚቀርቡት ብቻም ሳይሆን እንድ የሆኑት ከወፍ ዋሻዎቹ ነው፡፡

ሰዎቹ ቢካካዱም ዛፎቹ አይካካዱም! ሸዋ የነገስታቶቹ ዘር ነው! ሌላ ታሪክ አለ በቀጥታ ዛሬ ግንደ በረት አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ የእነ አጼ ንብለ ድንግል ዘሮች ናቸው! እንግዲህ የዘርን ጉዳይ ከአመጣችሁት ተረጋጉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጄኔቲክ ሴንሰስ ማድረግ ግድ ይለናል፡፡ ጥቁር እንጪኒ ሥያሜውን ያገኘው በሚኒሊክ አይምሰላችሁ! ከቀደሙት ነገስታት አንዱ ፈረሱን ያሰረበት ነው ብለው የዛው አካባቢ ነዋሪዎች ዛሬም ይነግሯችኋል፡፡
ዛሬ ሁሏም እየተነሳች ሕዝብን በጅምላ ወደእርሷ ቋት የምትጨምረው ለንግዷ እንዲያመቻት ነው እንጂ የእኔ ወግን ከሚል እንዳልሆነ ሁሉም ሊረዳው ይገባል፡፡ ማን ቢወልድ ማን ዘር ይሆናል፡፡ እንግዲህ ዘር ከተባለ የሸዋ አማራና የሸዋ ኦሮሞ ከማንም በላይ ዘር ናቸው፡፡ እስካሁንም እንዛው ይኖራሉ፡፡ ለመሆኑ ስታስቡት የኦሮሞነትና ዛሬ ደግሞ አማራ ነኝ ብሎ የተነሳው ማንነት አውን አማራ ኦሮሞ ለተባለው ሕዝብ ነው የሚሰራው? አንቀልድ! የማንም መጫወቻ አንሆንም! ከኢትዮጵያዊነት ያነሰ ሊያሰባስበን የሚችል አንዳች ነገር የለም የሴረኞች መተቀሚያ ከመሆን በቀር፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያና አካባቢዋ ሕዝብ ከሌላው ዓለም ሳይቀር እንድ የሚያደርገው የዘር ትስስር አለ፡፡ ይህን በአለፈው አሳይቻችሁ ነበር፡፡ ዛሬ እነ አብይ እያጣመሩ ያሉት ይህን ሕዝብ ነው፡፡ ሱማሌ፣ ጂቡቲ፣ ኤርትራ፣ ሱዳንና ኢትዮጵያ የአንድ ዘር መሠረት ያላቸው ሲሆኑ፡፡ በውስጥ ግን የበለጠ የሚቀራረቡ ከተባለ የሸዋ ኦሮሞ ዘሩ የሸዋ አማራ/ጉራጌ እንጂ ሀረር ወይም አርሲ እንዳልሆነ እቅጩን እነግራችኋለሁ፡፡ ቡድን ከተባለ ይህን ሕዝብ አንድ የሚያደርግ ቡድን የመስረት፡፡

ጎጃም ከጎንደር ሳይሆን ከወለጋ ጋር ይቀርባል፡፡ ሁለቱም የዳሞት ዘሮች ናቸው! እነዛ ዳሞት ጋፋት ምናምን ሲባሉ የነበሩ ዘሮች እኮ ቋንቋቸው ጠፋ እንጂ ዘራቸው አልጠፋም፡፡ የሆነ ሆኖ ዛሬ የሚወራለት የኦሮሞነትም በሉት አማራነት ወይም ሌላ ቡድን የእምቧይ ካብ እንደሆን አስተውሉ፡፡ ኦሮሚያ የተባለው ክልል ከኢትዮጵያ ውጭ ለብቻው ቢገነጠል በሳምንታት ውስጥ ዘጠኝ ትንንሽ እንደሚሆን እናውቃለን፡፡ ዛሬ ያለው የማስመሰል አንድነት ዓላማው ሌሎችን በጋራ ለማጥቃት እንጂ አንድ ሕልምና ግብ ያለው ማህበረሰብም ሆኖ አደለም፡፡ በተመሳሳይ አማራው እንደዚሁ ነው ከኦሮሞው ቢሻል ትንሽ ነው፡፡

መንግስት በአፋጣኝ መውሰድ ከሚገባቸው እርምጃዎች አንዱ ይህን ሆን ተብሎ ዜጎችን የቡድ መብት በሚል የግል መብትን እየደፈቀ ያለውን ቡድን ተኮር አመለካከትን ማፍረስ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ አሁን ያለውን ፌደራል አወቃቀር ማፍረስ ግድ ይላል፡፡ ወለጋ ከቦረና ጋር ፌደራል የሚሆንበት ምንም ዓይነት ዓመክኒዮዋዊ መሠረት የለውም ሴራዊ መሠረት እንጂ፡፡ ኦሮሞን ላለፉት 27 ዓመታት ሲነዱት የነበሩት ወለጋና አርሲ ነበሩ፡፡ ዛሬ ኦሮሞን በኦሮሞነት ሙጥኝ የሚሉትም እነዚሁ ናቸው! የኦሮሞ አንድነት ምናምን እያሉ የሚቀባጥሩትም! ዛሬ ለመጣው ለውጥ ግን ዋና ሚና የተጫወተው የዳጩ ዘር በሚል እንደ አማራው ሁሉ ሲገፋ የኖረው የሸዋ ኦሮሞ እንደሆን ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ የፌደራል መዋቅር በአዲስ መልክ የዋቀር፡፡

አስፈላጊ በሆነባቸው ቦታዎች ዛሬ በተለያየ ብሔር የተካለሉት በእንድ ላይ በማጣመር፡፡ ከሁሉም በፊት ግን ሸዋ ለብቻው ክልል ሆኖ የሁሉም መዳረሻ ሊሆን ግድ ይላል፡፡ የሰሞኑ የኦሮሞ አክራሪዎች ከተሞችን አስመስክቶ የሚያነሱት ሀሳብ ሌሎችን ለማግለል እንጅ በምንም መስፈርትና አመክንዮ የከተማው ነዋሪዎችን መብት በጥቅል የቡድን መብት በሚል ሊገፍፍ አይችልም፡፡ ዲሞክራሲ ከተባለ እንግዲህ ወሳኝ መሆን ያለበት በቦታው የሚኖረው ሕዝብ እንጂ በክልል ሥም እየተንጠራራ የሌላውን መብት ረግጦ የእኔ ክልል ነው በሚል አደለም፡፡ ሸዋ ግን ለብቻው ተከልሎ ኦሮምኛም አማርኛም እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ በወሳኝነት የሚነገሩ ቋንቋዎች የሥራ ቋንቋ የሚሆኑበት ይሆናል፡፡ የፌደራል መንግስቱ ሌሎች ቋንቋዎችን አስተናገደም አላስተናገድምም ሸዋ ግን አዲስ አበባን ጨምሮ እንደክልል ከአንድ በላይ ቋንቋ ክልል ይሆናል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሚያገባው የሸዋ ሕዝብ እንጂ በኦሮሞነት ከወለጋ ወይም ከቦረና ወይም በአማራነት ከጎጃም ወይም ከጎንደር አደለም፡፡ ከዛ በኋላ ክልሉን የሁሉም ሕዝብ ማዕከልና መዳረሻነትን በሚጋብዝ ሁኔታ ማስተዳደር ነው፡፡ የሸዋ የክልል ሀሳብ እኔ ዛሬ ያነሳሁት ሳይሆን አንዳንዶች ብዙ ሄደውበት ነበር፡፡ አሁንም አጥብቀው እንዲቀጥሉበት እላለሁ፡፡ ሸዋ ራሱን ችሉ ክልል ሲሆን የዘር ፌደራሊዝም ሳይወድ በግዱ እንክትክቱ ይወጣል፡፡ መቼም ኦሮሞን ለመከፋፈል እንደሚባል አውቃለሁ፡፡ እንዲህ ያለ ቀልድ የለም፡፡ 27 ዓመት ተዘፈነብን፡፡

ወለጋም ራሱን ይቻል ሀረርም ራሱን፣ ሌላውም ራሱን፡፡ በኦሮሞነት ሥም ብዙዎች ማንነታቸው ተረግጧል፡፡ ሸዋም በሸዋዎች ትተዳደር፡፡ ከጥንት ጀምሮ ሸዋ አሰባሳቢ ነው፡፡ መቼም አማራ ነኝ ያለው ሌላው ደብረብርሀን ተወሰደብኝ አይለንም፡፡ ከዛ አብን ደህና ሰንበት ማለት ነው፡፡ ያኔ በአማራ ሥም ጎጃምና ጎንደር ሲንቀሳቀስ እናያለን እስኪ፡፡ ቁልፉ ሸዋ ላይ ነው ሸዋን ኢትዮጵያን የሚወክል ክልል ማረግ ከቻልን የዘር ፖለቲካ ያበቃላታል፡፡ በሕዝብም ረገድ ሲታይ የዘርን ፖለቲካ ሊገላግለን የሚችል ሸዋ ነው! ልዑል እግዚአብሔር ለኢትዮጵያና ልጆቿ ጥበብንና ማስተዋልን ይስጥ! አሜን!

ሰርፀ ደስታ